# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ

የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

መመሪያ ቁጥር 78/2014

## መግቢያ

በሀገራችን እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለበርካታ ዓመታት ስር ሰዶ የቆየ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ የከተማችን ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ እያደረገ የመጣ መሆኑ እና ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ የሆነ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በከተማችን ማህበራዊና ኢኮኖሚየዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ለዘርፉ ልማት ትኩረት በመስጠት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የልማት ፖሊሲና ስትራተጂ ላይ ተመስርቶ የራሱ ፕሮግራምና ድጋፍ ፓኬጅ ተዘጋጅቶ በተመረጡ ዕድገት ተኮር ዘርፎች ላይ በማተኮር ለኢንተርፕራይዞች ድጋፍ መስጠት ተችሏል::

ስለሆነም ልማቱን ለማፋጠን የተከናወኑ ተግባራት በአብዛኛው በመንግስት ድጋፍ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን  በኢንተርፕራይዞች የተጠናከረና ከብልሹ አሰራር የፀዳ ተቋም ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ክፍተት ታይቷል፡፡ ኢንተርፕራይዞች በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባለመደራጀታቸው የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፤ የማሽነሪ አቅርቦት፤የዕውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም የገበያና የምርት ትስስር አገልግሎት  በአንድነት ለማከናወን እና ወጪን በመቀነስ አቅርቦታቸውን በመጨመር የምርት ጥራትና ምርታማነት ተወዳዳሪ መሆን ባለመቻሉ፤

በከተማችን የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ችግራቸውን በጋራ ለመፍታት፤ መልካም ዕድሎችን በጋራ ለመጠቀም፤ እንዲሁም መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እንዲደራጅ  በማድረግ አሁን የተገኙትን ጅምር ውጤቶች ይበልጥ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

*ይህ መመሪያ የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 78/2014 ተብሎ ይጠቀሳል፡፡*

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡

1. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ነው፡፡
2. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
3. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት የወረዳና የክፍለ ከተማ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽህፈት ቤት ነው፡፡
4. **"ተቋም"** ማለት ከማዕከል እስከ ወረዳ ያለውን የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት የመንግስት መዋቅር ነው፡፡
5. **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ የተደራጀ ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ነው፡፡
6. **"አንቀሳቃሽ"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ ተደራጅተው በማምረት፣ ምርትን በመሸጥ ወይም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የኢንተርፕራይዝ አባል ነው፡፡
7. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ እስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የካፒታል መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡
8. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የካፒታል መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) እስከ 500,000.00 (አምስት መቶ ሺ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001.00 (አንድ መቶ ሺ አንድ) እስከ 1.5 ሚሊዮን ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

9. **"የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት"** ማለት በአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፍ በንግድ ህጉ ከተደራጀ ኢንተርፕራይዝ ከወረዳ እስከ ማዕከል በየደረጃው በሚገኝ ኢንተርፕራይዞች በምርጫ የተወከለ ነው፡፡
10. **"የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ"** ማለት በአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፍ በንግድ ህጉ ከተደራጀ ኢንተርፕራይዝ ከወረዳ እስከ ማዕከል ከምክር ቤት አባላት  በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው የአመራር ስራ የሚሰራ አካል ነው፡፡
11. **"የህዝብ ክንፍ"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ እና አጋር ሆኖ የሚያገለግል የህዝብ አደረጃጀት ነው፡፡
12. **"አምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፍ"** ማለት ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ከተማ ግብርና፣ ንግድ እና አገልግሎት የስራ ዘርፍን የያዘ ነው፡፡
13. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
14. በዚህ መመሪያ ውስጥ **በወንድ** ፆታ የተገለፀው **የሴትንም** ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፡-

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፣ በስሩ ባሉት ተቋማት እና በጥቃቅንና አነስተኛ በተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ፡-

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት  በማደራጀት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ መብታቸውንና ግዴታቸውን በጋራ እንዲወጡ፤ብልሹ የሆነ አሰራርን በመታገል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ልማት ላይ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ነው፡፡

## 5. የመመሪያው አስፈላጊነት፡-

1. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማደራጀት ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል በማረጋገጥ መንግስታዊ ድጋፎችን እኩል ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ  ለመፍጠር፤
2. ያለ አግባብ የሚሰጡ የጥቃቅንና አነስተኛ ድጋፎች ብልሹ የሆነ አሰራር እና ተግባር የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ፤

3. በተቋሙ አሰራር ላይ ለሚስተዋሉ ችግሮች ግልጽነትና ተጠያቂነት ሥርዓት ለማስፈን፤
4. በተለምዶ ይሰሩ የነበሩ የአሰራር ክፍተቶችን በማሰወገድ ግልጽ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት፤
5. በመንግስት እና ኢንተርፕራይዞች መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ለማገልገል፤
6. በጥቃቅንና አነስተኛ የሚመረቱ ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲተዋወቁ ፣ የዕውቀት ፣ የክህሎት ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማድረግ፤
7. ኢንተርፕራይዞች ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር በመካከላቸው የውድድር መንፈስ እንዲኖር ማስቻል፤
8. ኢንተርፕራይዞች ችግራቸውን በጋራ ለመፍታት አቅማቸውን በጋራ በመጠቀም ከጠባቂነት መንፈስ እንዲላቀቁ ለማድረግ፤
9. ኢንተርፕራይዞች የሚገጥማቸውን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የገበያ ትስስር እና የምርት ትስስር በራሳቸው እንዲፈቱ ለማድረግ፤
10. ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ምርት በማምረት ኤክስፖርት በማድረግ እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

## የጥቃቅንና አነስተኛ የኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት የሚደራጁባቸው ዕድገት ተኮር ዘርፎች ፣ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለመወዳደር መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፣ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚደራጅባቸው ተቋማት ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለመምረጥ መሟላት ያለበት መስፈርት ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አደረጃጀት ፣ የስብሰባ ጊዜ እና ከተቋሙ ጋር ያለው ግንኙነት

6. **የጥቃቅንና አነስተኛ የኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት የሚደራጁባቸው ዕድገት ተኮር ዘርፎች፡-**
   1. የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፤
   2. የኮንስትራክሽን ዘርፍ እና የማዕድንና ቁፋሮ ዘርፍ፤
   3. የከተማ ግብርና ዘርፍ፤

4. የንግድ ዘርፍ፤
5. የአገልግሎት ዘርፍ፡፡

## 7. ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚደራጅባቸው ተቋማት፡-

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባለት ሲመረጥ ከአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፎች ሆኖ ንዑስ ዘርፉን መሰረት በማድረግ አባላት መመረጥ አለበት፡፡
2. በወረዳ ደረጃ ከአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፍ ከእያንዳንዱ ዘርፍ አምስት አምሰት አባላት በመምረጥ 25 አባላት ያሉት የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መደራጀት አለበት፡፡
3. በክፍለ ከተማ ደረጃ እንደ ወረዳው ብዛት ከእያንዳንዱ ወረዳ ከተመረጡ አምስት አባላት የዕድገት ተኮር ዘርፍ መሰረት የተመረጡ የክፍለ ከተማው የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መደራጀት አለበት፡፡
4. የቢሮው የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ከአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፎች በተመረጡ አምስት አባላት መደራጀት አለበት፡፡

## 8. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አደረጃጀት፡-

የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከጥቃቅንና አነስተኛ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መካከል ከአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፎች መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ አባላት የሚመረጥ አምስት አባላት ያሉት ሲሆን አደረጃጀቱ፡-

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፤
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ፤
3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሂሳብ ሹም፤
4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ፤
5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል፡፡

## 9. ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለመወዳደር መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፡-

1. ከአምስቱ እድገት ተኮር ዘርፎች በአንዱ የተደራጀ  በስራው ላይ ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
2. ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተሻለ እቅድ ማቀድና ፕሮግራም መቅረጽ የሚችል መሆን አለበት፡፡
3. የኢንተርፕራይዞችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመረዳት  ከአጋር አካላት ጋር ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ መሆን አለበት፡፡
4. በስራው ውጤታማ የሆነ እና ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

5. ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን ለመታገል ቁርጠኛ መሆን አለበት፡፡
6. ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚመረጠው የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 10. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለመምረጥ መሟላት ያለበት መስፈርት፡-

1. ከአምስቱ ዕድገት ተኮር ዘርፎች በአንዱ የተደራጀ በስራው ላይ ቢያንስ የአንድ ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
2. ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተሻለ እቅድ ማቀድና ፕሮግራም መቅረጽ የሚችል መሆን አለበት፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጥቅሞችን ማስጠበቅና ችግሮች በመፍታት ከአጋር አካላት ጋር ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡
4. በስራው ውጤታማ የሆነ እና ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡
5. ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን ለመታገል ቁርጠኛ መሆን አለበት፡፡
6. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚመረጠው አካል የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 11. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመን፡-

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ከተመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ለ3 /ሶስት/ ዓመት ማገልገል አለበት፡፡
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከተመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ለ3 /ሶስት/ ዓመት ማገልገል አለበት፡፡
3. የአገልግሎት ዘመናቸውን ሳይጨርሱ በተለያየ ምክንያት ከአባልነት የሚወጡ አባላት በሚኖሩት ወቅት የምክር ቤቱን ጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ በመጥራት በጎደሉት አባላት የመተካት ስራ መስራት አለበት፡፡

## 12. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ፡-

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የምክር ቤቱን እቅድ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የተቋሙን እቅድ መሰረት በማድረግ ያቀደውን እቅድ ማጸደቅ አለበት፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እየተገናኙ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተቋሙን እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡

3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

## 13. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ፡-

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እቅዱን በማዘጋጀት በየወሩ የስራ አፈፃፀሙን ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በታቀደው እቅድ መሰረት ሪፖርት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተቋም በማቅረብ ማስገምገም አለበት፡፡
3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንደ አስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 14. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተቋሙ ጋር ያለው ግንኙነት፡-

የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተቋሙን የህዝብ  ክንፍ በመሆን የሚሰራ ሲሆን፡-

1. ከወረዳ እስከ ማዕከል የጥቃቅንና አነስተኛ ምክር ቤት አባል በመሆን መስራት አለበት፡፡
2. በተቋሙ እቅድ ውይይት እና የእቅድ አፈፃፀም ላይ በመሳተፍ መገምገም አለበት፡፡
3. ከተቋሙ ጋር የክትትል፣ ድጋፍ እና የሱፐርቪዥን ስራዎችን በጋራ መስራት አለበት፡፡
4. በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በአካል በመገኘት ምልከታ ማድረግ አለበት፡፡
5. ከተቋሙ የህዝብ ክንፍ ከሆኑት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ማህበር፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች ማህበር እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካል ጉዳተኛ ማህበር ጋር በጋራ መስራት አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

## የተቋማት፣ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣን እና ተግባር

15. **የቢሮ ስልጣን እና ተግባር፡-**
    1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አደረጃጀት መመሪያ በማዘጋጀት በተዋረድ ለሚገኙ ተቋማት በማስተላለፍ እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡
    2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ የግብዓት ድጋፍ እና የግንዛቤ ስልጠና ይሰጣል፡፡
    3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለተቋሙ የህዝብ ክንፍ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርጋል፡፡
    4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡
    5. የተቋሙን ዕቅድ አፈፃፀም በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በውጤት ተኮር መመዘኛ መስፈርት መሰረት በመገምገም እንዲመዝኑ ያደርጋል፡፡
    6. በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ብልሹ የሆነ አሰራር ሲገጥማቸው ችግሮችን ተከታትሎ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡
    7. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡
    8. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማደራጀትና ዕውቅና በመስጠት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

16. **የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ስልጣን እና ተግባር፡-**
    1. ከማዕከል በወረደለት የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት ያደራጃል፣ በተዋረድም ለሚገኙ ተቋማት በማስተላለፍ እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡
    2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ የግብዓት ድጋፍ እና ግንዛቤ ስልጠና ይሰጣል፡፡
    3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለተቋሙ የህዝብ ክንፍ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርጋል፡፡
    4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ላይ

እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

5. የተቋሙን ዕቅድ አፈፃፀም በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በውጤት ተኮር መመዘኛ መስፈርት መሰረት በመገምገም እንዲመዝኑ ያደርጋል፡፡
6. በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ብልሹ የሆነ አሰራር ሲገጥማቸው ችግሮችን ተከታትሎ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡
7. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡
8. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማደራጀትና ዕውቅና በመስጠት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

17. **የወረዳ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባር፡-**

1. ከክፍለ ከተማ በወረደለት የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት ያደራጃል፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ የግብዓት ድጋፍ እና የግንዛቤ ስልጠና ይሰጣል፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለተቋሙ የህዝብ ክንፍ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርጋል፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡
5. የተቋሙን ዕቅድ አፈፃፀም በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በውጤት ተኮር መመዘኛ መስፈርት መሰረት በመገምገም እንዲመዝኑ ያደርጋል፡፡
6. በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ብልሹ የሆነ አሰራር ሲገጥማቸው ችግሮችን ተከታትሎ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡
7. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተጠናክሮ ስራውን እንዲሰራ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡
8. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማደራጀትና ዕውቅና በመስጠት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

18. **የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን እና ተግባር፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ለመረጣቸው ኢንተርፕራይዞች የበላይ ኃላፊ በመሆን ይሰራል፡፡

2. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ውስጥ የዕድገት ተኮር ዘርፎችን መሰረት በማድረግ የስራ አስፈፃሚ ኮሜቴ አባላትን ይመርጣል፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት የምክር ቤት የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ ያፀድቃል፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት የምክር ቤት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ገምግሞ ያፀድቃል፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት የምክር ቤት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ያፀድቃል፡፡
6. ከሒሳብ ሹሙ እና ከፀሐፊው የሚቀርቡትን ሪፖርቶች ይገመግማል ያፀድቃል፡፡
7. የዘርፍ ማህበራት የምክር ቤት ሒሳብ በውጪ ኦዲተር የኦዲት ሪፖርት እንዲሰራ ያደርጋል፡፡
8. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱን የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠራ ስብሰባዎችን ያደርጋል፡፡
9. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ውስጥ 1/3ኛው ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራላቸው ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፡፡

## 19. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣን እና ተግባር፡-

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ በማጸደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
3. የበጀት ዓመቱ የስራና በጀት እቅድ በማቀድ ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያፀድቃል፡፡
4. የበጀት ዓመቱ የስራና በጀት እቅድ በማቀድ በየደረጃው ለሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዕቅዱን በማቅረብ እንዲገመገም ያደርጋል፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ አፈፃፀም ገምግሞ ያፀድቃል፡፡
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት 1/3ኛው ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሳቢው አማካኝነት እንዲጠራ ያደረጋል፡፡
7. ከወረዳ እስከ ማዕከል ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ጋር በጋራ በመተባበር ስራዎችን ይሰራል፡፡
8. የተቋሙ የህዝብ ክንፍ ከሆኑት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ማህበር፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች ማህበር እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካል ጉዳተኛ ማህበር ጋር በጋራ በመተባበር ይሰራል፡፡

9. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሊያግዙ የሚችሉ የተለያዩ ቴክኒካል ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ከምክር ቤት አባላት ውስጥ ያቋቁማል፡፡
10. ከተቋሙ ጋር በመሆን በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ በጋራ በመሆን ይሰራል፡፡
11. የመስሪያ ቦታዎች ማስተላለፍና አጠቃቀም ላይ ፍትሃዊ እንዲሆን በጋራ ይሰራል፡፡
12. ለኢንተርፕራይዞች የተላለፉ መስሪያ ቦታዎች ዘርፉ የሚጠይቀውን ስታንዳርድ እንዲጠብቁ እና የመሰረተ ልማት ችግሮች እንዲፈታላቸው ክትትል ያደርጋል፡፡
13. በመስሪያ ቦታ የቆይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ በውላቸው መሰረት ተጠቅመው መውጣታቸውን ይከታተላል፡፡
14. በየክላሰተሩ ከተደራጁ የግቢ ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀት የመስሪያ ቦታዎች ለስራ ምቹ፣ ጽዱ እና አረንጓዴ እንዲሆን ይሰራል፡፡
15. የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር ላይ ያለአግባብ ለመሸጋገርና ላለመሸጋገር የሚፈልጉ ኢንተርፕራዞችን ለተቋሙ እየተከታተለ መረጃ ይሰጣል፡፡
16. በተቋሙ ለኢንተርፕራይዞች የሚፈጠሩ የገበያና የስራ ትስስር ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መሰራታቸውን ክትትል ያደርጋል፡፡
17. ለኢንተርፕራይዞች የሚዘጋጁ ኢግዚቪሽንና ባዛር ላይ የእኩል ተጠቃሚነት መሰረት ያደረገ አሰራር እየተሰራ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡
18. ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸው ምርቶች ደረጃ ምደባ እንዲወጣላቸው ክትትል ያደርጋል፡፡
19. ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት ኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶች እንዲያመርቱ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡
20. ኢንተርፕራይዞች የሚገጥማቸውን የግብዓት አቅርቦት ችግር በጋራ በመሆን እንዲፈቱ ጥረት ያደርጋል፡፡
21. ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው የዕውቀት፣ክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርጉ ይሰራል፡፡
22. የተቋሙን ዕቅድ አፈፃፀም ይገመግማል ፣ በውጤት ተኮር መመዘኛ መስፈርት መሰረት ከአጋር ህዝብ ክንፍ ጋር በመሆን የስራ ውጤት ምዘና ያደርጋል፡፡
23. ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን እየተከታተለ

እንዲስተካከሉ መረጃ ይሰጣሉ፡፡

24. በተጓደሉ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት እየተከታተሉ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

## 20. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ስልጣን እና ተግባር፡-

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለመረጠቸው ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ለአስፈፃሚ ኮሚቴ አወያይቶ ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተሰጡትን ስልጣን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
4. በየደረጃው ለሚገኝ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክር ቤት ላይ በመወከል ይሳተፋል፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የበጀት እና የፋይናንስ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
6. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ገቢ ለማሳደግ የገቢ ምንጮችን መፍጠር እና የማፈላለግ ስራ ይሰራል፡፡
7. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
8. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፀሐፊና ሒሳብ ሹም ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ደብተር እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡፡

## 21. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ስልጣን እና ተግባር፡-

1. የስራ አስፈፃሚ ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለመረጣቸው ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
2. የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ መዝገቦችን ያደራጃል፣ ይይዛል ፡፡
3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጽ/ቤት ያደራጃል፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

6. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰብሳቢና ሒሳብ ሹም ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ደብተር እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡፡
7. የምክር ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

22. **የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሂሳብ ሹም ስልጣን እና ተግባር፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱን የገንዘብ ገቢና ወጪ ስራዎችን ይሰራል፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱን የበጀት ዓመቱን ሂሳብ ሪፖርት በተያዘለት ጊዜ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡
3. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰብሳቢና ፀሐፊ ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ደብተር እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡፡
4. የምክር ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

23. **የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ ስልጣን እና ተግባር፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቱን የገንዘብና ንብረት ባለቤት በመሆን መዛግብት ይይዛል፡፡
2. በምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ገንዘብና ንብረት እንዲያንቀሳቅስ ሲፈቀድለት ወጪና ገቢ ያደርጋል፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሒሳብ ወጪና ገቢ በውጪ ኦዲተር ኦዲት ያስደርጋል፡፡
4. የምክር ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

24. **የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ስልጣን እና ተግባር፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰራቸውን ስራዎች ክትትል ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ተሳትፎ ያደርጋል፡፡
3. የምክር ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት

ያከናውናል፡፡

# ክፍል አራት

## የተቋሙ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መብቶች እና ግዴታዎች

25. **የተቋሙ መብት፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን በህዝብ ክንፍነት መጠቀም ይችላል፡፡
2. በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ብልሹ የሆኑ አሰራር ሲፈጠር ማስተካከል ይችላል፡፡
3. ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሰብሰብ ይችላል፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እቅድ አፈፃፀም መገምገም ይችላል፡፡

26. **የተቋሙ ግዴታ፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚመራበት የአደረጃጀት መመሪያ በማውጣት ማደራጀት አለበት፡፡
2. ለዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ማህበሩን ለማጠናከር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መስራት አለበት፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስራዎቻቸውን በአግባቡ እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን በህዝብ ክንፍነት በመጠቀም በ6 /ስድስት/ ወሩ ስራን ማስመዘን እና እቅድ አፈፃፀሙን ማስገምገም አለበት፡፡
5. በዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አባላት አማካኝነት የሚቀርቡ ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን በፍጥነት መፍታት አለበት፡፡
6. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለሚሰሯቸው ስራዎች ዕውቅና መስጠት አለበት፡፡

27. **የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መብት፡-**

1. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ እና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በመመሪያው መሰረት መደራጀት ይችላል፡፡

2. የተቋሙን ዕቅድ፣ ሪፖርት፣ መመሪያዎች እና የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማወቅና መጠቀም ይችላል፡፡
3. ከተቋሙ የሚፈልገውን መረጃ እና ድጋፍ ማግኘት ይችላል፡፡
4. የዘርፍ ማህበሩ ምክር ቤት ያለምንም ጣልቃ ገብነት እራሱን በራሱ መምራት እና ማስተዳደር ይችላል፡፡
5. የዘርፍ ማህበሩ ምክር ቤት የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡
6. የዘርፍ ማህበሩ ምክር ቤት በራሱ የገቢ ምንጮችን ማፈላለግ ይችላል፡፡
7. የዘርፍ ማህበሩ ምክር ቤት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን መምረጥ እና መሻር ይችላል፡፡

## 28. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ግዴታ፡-

1. በዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አደረጃጀት መሰረት መስራት አለበት፡፡
2. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚመራበት የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በማውጣት መመራት አለበት፡፡
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እቅዱን በማሳወቅ አፈፃፀም በሪፖርት ለተቋሙ መስጠት አለበት፡፡
4. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ማመቻቸት አለበት፡፡
5. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ መወጣት አለበት፡፡
6. ለተቋሙ የህዝብ ክንፍ በመሆን ማገልገል አለበት፡፡
7. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተቋሙ ጋር በጋራ በመሆን የሚገጥማቸውን ችግሮችና ብልሹ የሆኑ አሰራሮችን መፍታት አለበት፡፡
8. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚነት ላይ መስራት አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

29. **የተጠያቂነት ሥርዓት፡-**

    1. ማንኛውም የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ፈጻሚ ወይም ኃላፊ ይህን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡
    2. ማንኛውም የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባል ይህን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

30. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች፡-**

    ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ማንኛውም መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

31. **መመሪያውን ስለማሻሻል፡-**

    ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

32. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-**

    ይህ መመሪያ ከዛሬ ሰኔ/2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሰኔ/ 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**